
# ጎዞ ወደ ቶክዮ

## ለ2025 የአለም አትሌቲክስ ሻምፒዮና በስፖርት ንፁህ ታእማኝነት መመርያ

(13-21 ሴምቴበር፣ቶክዮ፣ጃፓን)



aiu_athletics

aiu_athletics

aiu_athletics

community@athleticsinetgrity.org

www.athleticsintegrity.org

ይህ በራሪ ወረቀት በ2O25 የአለም አትሌቲክስ ሻምፒዮና (የአለም አትሌቲክስ ሻምፒዮና (WCH) ቶኪዮ 25) ለሚሳተፉ አትሌቶች እና የአትሌቶች ድጋፍ ሰጭ አካላት አስፈላጊ መረጃን ይሰጣል።

ይህ መረጃ ከአለም አትሌቲክስ ሻምፒዮና (WCH) ቶኪዮ 25 በፊት፣ ወቅት እና በኋላ ባለው የንፁህ የስነምግባር ህግ እና ፀረ-አበረታች ቅመሞች ላይ በትክክለኛ መስመር ላይ እንዲቆዩ ይረዳዎታል።

Integrity Code of Conduct
Anti-Doping Rules



athleticsintegrity.org/road-to-tokyo

# አትሌቲክስ ኢንተግሪቲ ዩኒት ማን ነው(AIU)?

አትሌቲክስ ኢንተግሪቲ ዩኒት (AIU) በአትሌቲክስ ስፖርት የዶፒንግና ዶፒንግ ያልሆኑ ጉዳዮች ጨምሮ ሁሉንም በስፖርት ንፁህ የታእማኝነትን ጉዳዮችን ለመፍታት በዓለም አትሌቲክስ የተቋቋመ ራሱን የቻለ አካል ነው።

## እኛ .....

መሳተፍ
በመደገፍ
አቅም በማጉልበት
በማሳወቅ
ትምህርት ማስተማር
መግባባት
ምርመራ
የማጣራት ስራ
ጥፍተኛን መቅጣት



# የመከባበር ሀይል

በ2023 በቡዳፔስት የዓለም ሻምፒዮና ውድድር ላይ የስፖርቱን ንጹሕ ታማኝነት አቋም ለመጠበቅ ራስን፣ ሌሎችንና ደንቦችን ማክበር አስፈላጊ መሆኑን ለማጉላት የአክብሮት ኃይል ዘመቻ ተጀመረ።

ይህ ዘመቻ በመላው የአትሌቲክስ ማኅበረሰብ ላይ ከፍተኛ ተጽዕኖ ያሳደረ ከመሆኑም በላይ ከፍተኛ ተሳትፎ ተደርጓል ።

በአለም አትሌቲክስ ሻምፒዮና (WCH) ቶኪዮ 25 ይህ ዘመቻ በዕለት ተዕለት ተግባራት አማካኝነት ሌሎችን የማክበርን አስፈላጊነት ለማጉላት ይዳብራል ።
በአለም አትሌቲክስ ሻምፒዮና(WCH) ቶኪዮ25 በምናደርጋቸው የማሳወቅ እንቅስቃሴዎቻችን ትኩረት ይህ ይሆናል, የአክብሮት ኃይል ለእርስዎ ምን ትርጉም እንዳለው ለመወያየት ከእኛ ጋር እንዲገናኙ እንጋብዝዎታለን፣ እንዲሁም ስለ ሁሉም የአትሌቲክስ ታማኝነት ርዕሰ ጉዳዮች እኛን በአካል በመገኘት በምናደርገው ድጋፍ ተጨማሪ መረጃን ያግኙ።

ከመስከረም 1 እስከ 11 ባለው ጊዜ ውስጥ በሺናጋዋ ፕሪንስ ሆቴል (የቡድኑ ሆቴል)እንዲሁም በአኔክስ ታወር 5ኛ ፎቅ ላይ እኛን ማግኘት ትችላላችሁ።




የዓለም አትሌቲክስ አትሌቶች ኮሚሽን አባላት፣ አይሻ ፕሩት-ሊር እና ዳም ቫለሪ አዳምስ በቡዳፔስት በተካሄደው የ2023 የዓለም አትሌቲክስ ሻምፒዮና ወቅት በዳሳችን ተገኝተው ነበር።

# የፀረ-አበረታች ቅመሞች ፕሮግራም በቶክዮ

ከአለም አትሌቲክስ ሻምፒዮና (WCH) ቶኪዮ 25 በፊት ቶክዮ እንደደረሱ በቡድኑ ሆቴል ውስጥ ለቅድመ ውድድር ምርመራ ሊመረጡ ይችላሉ
ከተመረጣችሁ፣ በቡድን ሆቴል ማዕከላዊ ወደሚገኘው የዶፒንግ መቆጣጠሪያ ጣቢያ እንድትሄዱ ትጠየቃላችሁ ።

በአለም አትሌቲክስ ሻምፒዮና (WCH) ቶኪዮ 25 ወቅት ኤአዩ በሻምፒዬና ውድድር ወቅት በስቴድየምና ከስቴድየም ውጪ ምርመራዎችን ያደርጋል
የቅድመ ውድድር ምርመራ ቢሰራላችሁም ባይሰራላችሁም በውድድር ቦታ ላይ ልትመረመሩ ትችላላችሁ

ከአለም አትሌቲክስ ሻምፒዮና (WCH) ቶኪዮ 25 በኋላ እንደተለመደው በ AIU, በብሄራዊ ፀረ-ዶፒንግ ድርጅታችሁ (NADO) እና በሌሎች ከሀገር ውጪ በሚገኙ NADOs አማካኝነት ልትመረመሩ ትችላላችሁ።

# በውድድር ውስጥ እና ከውድድር ውጪ የጊዜ ወቅት

ምንም እንኳን የወሰዳችሁት ንጥረ ነገር ከውድድር ውጪ ሆኖ ፣ ንጥረ ነገሩ ግን በውድድር ውስጥ የተከለከለ ከሆነ በሰጣችሁት ናሙና ላይ ቢገኝ ቅጣት ሊደርስባችሁ ይችላል።

ለዚህ ነው በውድድር ውስጥ እና ከውድድር ውጪ
የጊዜ ወቅት ያለውን ልዩነት ማወቅ
በጣም አስፈላጊ የሆነበት ምክኒያት አንዱ የሆነው።

| በውድድር ውስጥ የጊዜ ወቅት | ከውድድር ውጪ የጊዜ ወቅት |
|---|---|
| አትሌቱ ሊወዳደር ከተያዘለት የውድድር የጊዜ ሰሌዳ ከውድድሩ ቀን በፊት 23:59 ሰዓት ጀምሮ እስከ ውድድሩን ከጨረሰ በኃላና የናሙና መሰብሰቢያ ሂደቱ እስኪያልቅ ያለው ጊዜ ነው። | ከውድድር ጊዜ ውጪ የሆነ ማንኛውም አይነት የክፍለ ጊዜ ሲሆን ይህ ማለት በሁሉም ጊዜያት ማለት ነው። |
| ቅድመ ውድድር ክፍለ ጊዜ ማለት የውድድር መርሀ ግብሩ ከመጀመሩ በፊት ያለው ሲሆን ፣ ይህም የሚጀምረው ወደ ውድድር ስፍራ ማደርያ ከደረሱ ጊዜ ጀምሮ ነው ። በዚህን ጊዜ ከውድድር ውጪ ያለው የምርመራ ህግ ተፈፃሚነት ይኖረዋል። | |

# የተከለከለው ዝርዝር

የ2025 የዋዳ የተከለከለው ዝርዝር በቶኪዮ 2025 በተካሄደው የዓለም ሻምፒዮና ላይ ይመለከታል ። ይህ ዝርዝር በውድድርም ሆነ ከውድድር ውጪ የተከለከሉ ሁሉንም ንጥረ ነገሮች እና ዘዴዎች ይዟል።

## በህመም ምክኒያት የተከለከሉ ንጥረ ነገሮችን በፈቃድ መጠቀም የሚያስችል ስርዓት (TUE)

በህመም ምክኒያት የተከለከሉ ንጥረ ነገሮችን በፈቃድ መጠቀም (TUE) አስፈላጊ መሆኑን የሚያረጋግጥ ሕጋዊና የተመዘገበ የሕክምና ማስረጃ ማቅረብ ከቻሉ የተከለከለ ንጥረ ነገር ወይም ዘዴ መጠቀም ይፈቅዳል።

በቶኪዮ 2025 የሚወዳደሩ አትሌቶች በሙሉ ኢንተርናሽናል አትሌት ተብለው ስለሚወሰዱ በህመም ምክኒያት ማንኛውም አይነት የተከለከለ ንጥረ ነገር ወይም ዘዴ ከመጠቀማቸው በፊት የተረጋገጠና የሚሰራ በህመም ምክኒያት የተከለከሉ ንጥረ ነገሮችን ለመጠቀም ፈቃድ(TUE) ሊኖራቸው ይገባል።

በሀገራችሁ ናዶ የተሰጠ የTUE ፈቃድ በኤአዩ ለማረጋገጥ ወይም እውቅና እንዲኖረው እስከ ኦገስት14 የቶኪዮ 2025 አለም ሻምፒዬና ውድድር ከመጀመሩ 1 ወር በፊት ) በዚህ አድራሻ tue@athleticsintegrity.org. ማሳወቅ አላባችሁ

በህመም ምክኒያት የተከለከሉ ንጥረ ነገሮችን ለመጠቀም ፈቃድ(TUE) እንደሚያስፈጋችሁ ካረጋገጣችሁ፣ የተወሰነውን የማመልከቻ ሂደት በመከተል ማመልከቻችሁን በተቻለ ፍጥነት ወደ ኤአዩ አቅርቡ።

athleticsintegrity.org/know-the-process/therapeutic-use-exemptions

# መገኛ አድራሻ

በቶኪዮ 2025 አለም ሻምፒዬና ውድድር ላይ በተመዘገበ የምርመራ ቋት ስር የሚገኙ አትሌቶች የመገኛ አድራሻ መረጃቸውን እንደበፊቱ ማሳወቅ መቀጠል አለባቸው።

አትሌቱ የሚሰጠው መረጃ ትክክልና ወቅታዊ መሆኑን ማረጋገጥ የአትሌቱ ሀላፊነት ነው።

## የመገኛ አድራሻ መረጃዎች የሚከተሉትን ያካትታል

- ዕለታዊ የማደርያ ቦታ
- ዕለታዊ ለምርመራ ብቻ የሚመደብ የ60-ደቂቃ ጊዜ
- የውድድር መርሃግብር መረጃ
- መደበኛ ተግባራት( ምሳሌ፡- የልምምድ መርሃ ግብር)
- የጉዞ መርሃ ግብር መረጃ

በምርመራ ቋት ስር የሌሉ አትሌቶች በቶኪዮ 2025 አለም ሻምፒዬና ውድድር ላይ የመገኛ አድራሻ ማሳወቅ አይጠበቅባቸውም


| ወደ ቶኪዮ 2025 አለም ሻምፒዬና ለሚሄዱ በምርመራ ቋት ስር ለሚገኙ አትሌቶችቁልፍ ማስታወሻዎች | |
|---|---|
| ለቶኪዮ 2025 አለም ሻምፒዬና መድረሻ | ለውድድሮች፣ ሚኒማ ለማምጣት ፣ወደ ልምምድ ካምፕ የምትጓዙ ከሆነ የመገኛ አድራሻችሁ ወቅታዊና ትክክለኛ መሆኑን እርግጠኛ ይሁኑ |
| ቶክዮ እንደደረሳችሁ፣ቶኪዮ 2025 አለም ሻምፒዬና ከመጀመሩ በፊት | የክፍል ቁጥራችሁን፣ የልምምድ እና የውድድር መርሃ ግብር መረጃችሁን እንደደረሳችሁ ወቅታዊ የመገኛ አድራሻችሁን ሙሉ |
| በቶኪዮ 2025 አለም ሻምፒዬና ወቅት | በሁሉም የመገኛ አድራሻ መረጃ ዘርፍ ያሉ መረጃዎች ትክክል መሆናቸውን አረጋግጡ። ለውጦች እንዳሉ ባወቃችሁበት ወቅት በፍጥነት ወቅታዊ መረጃዎችን ያሳውቁ |
| ቶኪዮ 2025 አለም ሻምፒዬና በኋላ | እንደተለመደው የመገኛ አድራሻ ማሳወቅ |

# ውድድር ማጭበርበር

በውድድር ውጤት ላይ ተጽዕኖ ለማሳደር ወይም የአንድን የስፖርት ውድድር ወይም ማንኛውንም የስፖርት ተፈጥሯዊ ሂደትን ለማወክ ወይም ለመቀየር የሚደረገውን ማንኛውንም ጥረት ይመለከታል ።

ይህም ውጤቶችን መቀየርን፣ ውጤቶችን ማስተካከልን፣ መሣሪያዎችን መለወጥን፣ በሙስና መሳተፍን፣ በውስጥ ያሉ መረጃዎችን ማካፈልን ሊጨምር ይችላል።

እንዲህ ዓይነቱ ድርጊት የሚፈፀመው ለገንዘብ ጥቅም፣ ለፉክክር ወይም ለውጪያዊ ተጽዕኖ ሲባል ሊሆን ወይም ላይሆንም ይችላል።



# በቶኪዮ 2025 አለም ሻምፒዬና ላይ

እባክዎን በማንኛውም አጋጣሚ የምታውቃቸውን ማናቸውንም አቀራረቦች በጋያችሁት የመጀመርያ እድል ማንነታችሁ ሳይታወቅ የእኛን የሪፖርት ጣቢያዎች በመጠቀም ለማንኛውም የኤአዩ ሰራተኞች ወይም ማንኛውም አባል ሪፖርት አድርጉ

ለሚደረገው ማንኛውም አይነት የማጣራት ሂደት ላይ ተባባሪ ይሁኑ

በቶኪዮ 2025 አለም ሻምፒዬና ላይ ለእራሳችሁም ሆነ ለሌሎች ለመጥቀም ሲባል ምንም አይነት ውጤት መቀያየር ሂደት ውስጥ መሳተፍ የለባችሁም

ከውድድር ማጭበርበር ወይም ማንኛውም አይነት ሙስና ጋር በተያያዘ የሚመጣ ጥቅም ፍለጋ ፣መሻት ወይም ጥቅም መስጠት የለባችሁም

በራሳችሁ የውድድር ዘርፍ ወይም ሌላ ዘርፍ መወራረድ የለባችሁም እንዲሁም ሌሎችን እናንተን በመወከል እንዲወራረዱ አትጠይቁ

የውስጥ መረጃችሁን ለሌሎች አታካፍሉ( ስለ አትሌቶች ጉዳት ለሌሎች አለመንገር የመሳሰሉትን)

# የጫማ ህጎች

የአለም አትሌቲክስ ጫማ ህጎች ለውድድር መደረግ የሚችሉትን ጫማዎች በህጉ ደንግጓል፡፡

የተፈቀደ ጫማ እዚህ ላይ ማረጋገጥ ይቻላል፡፡

certcheck.worldathletics.org

## ከቶኪዮ 2025 አለም ሻምፒዮና በፊት

- ውጤትቶ እንዲቆጠር የሚያረጉትን ጫማ በቅድሚያ ማሳየቶን ያረጋግጡ!
- የምወዳደሩበት የጫማ ዓይነት ለይታችሁ ለማወቅና በተፈቀደለት የጫማ ዝርዝር ውስጥ እንዲካተቱ ለማድረግ የጫማውን መገለጫ ዝርዝር መረጃ መሙላት ያስፈልጋችኋል፡፡
- በህክምና ምክኒያት ጫማችሁ መስተካከል ካለበት ፈቃድ እንዲሰጣችሁ ቀድማችሁ አመልክቱ

## በቶኪዮ 2025 አለም ሻምፒዮናወቅት

- ገና በመስራት ያለ ወይም የማይታወቅ ጫማ አታድርጉ
- ከውድድራችሁ በኃላ የጫማ ቁጥጥር ሊኖር ስለሚችል የአትሌቲክስ ጫማችሁን ከራሳችሁ ጋር አድርጉ፡፡

ለተጨማሪ መረጃ ወይም በተደጋጋሚ የሚጠየቁ ጥያቄዎችን ለማየት በ rules@worldathletics.org ያግኙን

Frequently asked questions

# የአትሌቶችን ደህንነት ማስጠበቅ

ሁሉም ሰው የሚከበርበትና ከፍ ያለ ግምት የሚሰጠው አስተማማኝና ጥሩ አቀባበል የሚደረግበት አካባቢ መፍጠር የአትሌቶች ደህንነት ጥበቃ (Safeguarding) ወሳኝ ነገር ነው ።
ሁሉም ሰው በአትሌቲክስ ውድድሮች ላይ የሚፈጸመውን በደል፣ ጥቃት ወይም ብዝበዛ የመከላከል ኃላፊነት አለበት።

## ከቶኪዮ 2025 አለም ሻምፒዬና በፊት

ሁሉም አትሌቶችና ደጋፊ አካላት መልካም አከባቢ ለመፍጠር በውድድሩ የአትሌቶችን ደህንነት ለማስጠበቅ(Safeguarding) ያወጣውን መመርያና ለመተግበር ያፀደቀውን ፖሊሲ ማንበብ አለባቸው።
Safeguarding Policy

## በቶኪዮ 2025 አለም ሻምፒዬና ወቅት

የዓለም አትሌቲክስ የአትሌቶች ደህንነት ጥበቃ (Safeguarding) ባለሙያ ማንኛውም አይነት የደህንነት ጉዳይ ካለ ለመስማት የሚገኙ ሲሆን አስፈላጊውን እርምጃ ተግባራዊ እንዲሆን ለማድረግ ዝግጁ ነው።
safeguarding@worldathletics.org



# ሪፖርት በማድረግ የእርሶን ድርሻ ይወጡ

አትሌትም ሆኑ የአትሌት ደጋፊ፣ ለራሶት ሆነ ለሌሎች አትሌቶች ያላችሁ ክብር እንዲሁም ደንቦቹ ንጹህ፣ አስተማማኝና ፍትሃዊ የአትሌቲክስ ውድድሮችን እንድንቀጥል የሚረዱን ወሳኝ ነገሮች ናቸው።

የስፖርቱን ታማኝነት ለመጠበቅ አንዱ መንገድ ምንም እንኳን ጉዳዩ ትልቅ ወይም ትንሽ ቢሆን ታማኝነትን የሚፃረሩ ድርጊቶችን ማሳወቅ ነው ይህ መረጃ በስፖርታዊ እንቅስቃሴያችን ውስጥ የስፖርት ታማኝነት  ጥሰትን ለመለየት አስፈላጊ ሊሆን ይችላል.

አዲሱ የሪፖርት ወይም ማሳወቅያ መሣሪያችን አስተማማኝ ሲሆን፣ከተጠቃሚዎች ጋር ቀጥተኛ የሐሳብ ልውውጥ በማድረግ የሚያሳስባቸውን ነገር በምሥጢር ለመግለጽ ያስችላል ።

ይህ የሁለትዮሽ የሐሳብ ልውውጥ አስፈላጊ ነው ምክንያቱም ስለ ጉዳዩ የተሟላ ግንዛቤ እንድናገኝና ጠቃሚ አስተያየት እንድንሰጥ ያስችለናል።

## ማንነታችሁ ሳይታወቅ [athleticsintegrity.org/make-a-report](athleticsintegrity.org/make-a-report) ማሳወቅ ትችላላችሁ

"

## የስፖርቱን ንጹሕ ታአማኝነት አቋም ለመጠበቅ እና ንጹሕ ታአማኝነት አቋማችንን ለመጠበቅ የታቀዱትን ደንቦችእና ሥርዓቶች ለመረዳት እያንዳንዱን አጋጣሚ ለመጠቀም ሀላፊነትን መውሰድ አለብን።

Dame Valerie Adams
የዓለም አትሌቲክስ አትሌቶች ኮሚሽን ሰብሳቢ

